# ምርጫ መጣ፤ ረበሻ ውጣ

ክፍል ሁለት

ኢብሳ ነመራ

09-18-14

በዚሁ ርዕስ ባቀረብኩት ክፍል አንድ ፅሁፍ የ2007ን መግባት መነሻ በማደረግ በዚህ አመት ከሚካሄደው ምርጫ ጋር በተያያዘ የገገርውን ፓርቲ ቁመናና አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ያወጣውን መግለጫ ይዘት ተመልክተናል። በክፍል አንደ እንደተመለከትነው፣ "ምርጫ መጣ ፕሬስ ውጣ" በሚል መጪውን ምርጫ አስመልክቱ ባቀረበው ቧልት የተነሳው የአንድነት መግለጫ፣ በማያያዝ ባለፈው ዓመት "የሚሊየኖች ድምፅ ለነፃነት" እንዲሁም "የእሪታ ቀን" በሚል ሥያሜ ያካሂዳቸውን እንቅስቃሴዎች አስታውሶ ወደማወደስ ተሸጋግሯል።

እርግጥ ነው አንድነት በ2006 ዓ/ም "የሚሊየኖቸ ድምፅ ለነፃነት" እና "የእሪታ ቀን" የሚል ሥያሜ የተሰጣቸውን እንቅስቃሴዎች ለማድረግ መሞከሩን ሰምተናል። የሚሊየኖቸ ድምፅ ለነፃነት የተሰኘው የአንድነት ዘመቻ በሕዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት የፀደቀውን የፀረሽብርተኝነት ሕግ መቃወም ላይ ያተኮረ ነበር።

አንድነት በዚህ እንቅስቃሴው ኢትዮጵያ የፀረሽብርተኝነት ህጉን ማፅደቅ ያስፈለጋት፣ የተጋረጠባትን ቅርብና ደራሽ የሽብር ጥቃት ለመከላከል መሆኑን፣ እንዲሁም ሽብርተኝነት ዓለም አቀፍ ሥጋት እየሆነ በመምጣቱ የአፍሪካ ህብረትና የተባበሩት መንግስታት የፀረሽብር ሥምምነት ሕጉን እንድታወጣ የሚያስገድዳት መሆኑን ከግንዛቤ ማስገባት አልፈለገም። ይህ ኢትዮጵያ ያፀደቀችው ህግ ሌሎች ሃገራት ካወጡት መሰል ህግ ጋር ተመሳሳይና የሰብአዊ መብት ጥሰት ሊፈፀም የሚችልበትን መንገድ በመዝጋት ረገድ ከአንዳንድ ዴሞክራሲያዊ ከሚባሉ ሃገራት ህግ የተሻለ መሆኑንም አንደነት ማስታወስ አልፈለገም። የፀረሽብርተኝነት ህጉን የተቃወመው አንዳችም አሳማኝ ማብራሪያ ሳያቀርብ በደፈናው ነበር።

ይህን ያደረገው ባለማወቅ ነው ብሎ መውሰድ ሥህተት ላይ ይጥላል። የተቃወመው ሆን ብሎ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የሸብር ጥቃት ለመፈፀም በይፋ አውጀው የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ጥቂት ደጋፊዎችና በቅርቡ የተቀፈቀፉ የሽብርተኝኝነት ሌላኛው ገፅታው የሆነው የሃይማኖት አክራሪነት አመለካከት ጀሌዎችን ጭብጨባ ለመሸመት የሚያስችል ወቅቱ የፈጠረው ቀልብ ሳቢ አጀንዳ ሆኖ ስላገኘው ነው።

ከ2004 ጀምሮ በተለይ በአዲሰ አበባና ሌሎች አክራሪዎቸ የጂሃድ ጦርነት ለማካሄድ መደላድል በጣሉባቸው ጥቂት አካባቢዎቸ የአክራሪነት እንቅስቃሴ ይፋ መውጣቱንና ጀሌዎች ማፍራቱን ልብ በሉ። አንድነት ይህ የተወሰኑ መሪዎቻቸው በቁጥጥር ሥር ውለው በፀረሽብርተኝነት ህጉ ክስ የተመሰረተባቸውን የአክራሪነት እንቅስቃሴ ጀሌዎች ድጋፍ ፍለጋ ነው የፀረሽብርተኝነት ህጉን የተቃወመው። ለግዜው አጨብጫቢ ማግኘቱን እንጂ፣ አክራሪነት ለዘለቄታው በሃገሪቱ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አደጋ ምንም አላሳሰበውም።

በዚህ አኳኋን የሚሊየኖች ድምፅ ለነፃነት በሚል ስያሜ የፀረ ሽብርተኝነት ህጉን አሰርዛለሁ ብሎ የተነሳው አንድነት፣ ለዚህ ተግባራዊነት አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሃገሪቱ ከተሞች የተቃውሞ ሰልፎች ጠርቷል።ይሁን እንጂ አክራሪነት መሰረቱን በጣለበት ደቡብ ወሎ አካባቢ ያካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ በመጠኑ ሲሳካለት በተቀሩት የሃገሪቱ አካባቢዎች መና ቀርቷል። በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ለተቃውሞ ይወጡበታል ያለባቸው አካባቢዎች ጥቂት መቶዎች፣ በአስራ ሺህ ይወጣባቸዋል የተባለባቸው አካባቢዎች ደግሞ አስርና ሀያ ሰዎች ነበር የወጡት። ጭራሽ አንድም ሰው ባለመገኘቱ የፎረሹ የተቃውሞ ሳልፎችም አሉ።

የአንድነት የፀረሽብርተኝነት ሕጉን የማሰረዝ እንቅስቃሴ ከተቃውሞ ሰልፍ በተጨማሪ የሚሊየን ሰዎችን የድጋፍ ፊርማ የማሰባሰብ ፕሮግራምም ነበረው። ይህ የሚሊየኖች ፊርማ የማሰባሰበ እንቅስቃሴም እንዲሁ ከወሬ ሳያልፍ መና ቀርቷል። እርግጥ አንድነት በመጨረሻ ላይ በኦንላይን (በኢንተርኔት) በተሰበሰበ ፊርማ ግቤን አሳክቻለሁ ብሏል። በኢነተርኔት የተሰባሰበ ድጋፊ አንድ ሰውም ሊያደርገው ሥለሚችል ተአማኒነት የሌለው በመሆኑ የፊርማ ማሰባሰቡ እንደከሸፈበት ከማሳየት ያለፈ የጠቀመው ነገር አልነበረም።

እንግዲህ አንድ ሕግ የሚሰረዘው ወይም የሚሻሻለው፣ ይህን አስመልክቶ በሕገመንግስቱ ላይ በሰፈሩ ድንጋጌዎች ብቻ ሆኖ ሳለ፣ ሕገመንግስቱን በሚፃረር አኳኋን የተቃውሞ ስልፍንና ፊርማ ማሰባሰብን ባካተተ “ሕዝባዊ ንቅናቄ” የፀረ ሽብር ሕጉን አሰርዛለሁ ብሎ የተነሳው አንድነት ይህን ማድረግ ሳይችል ፎርሾ መቅረቱን እናስታውሳለን፤ በ2006 ዓ/ም።

አንድነት የፀረሽብርተኝነት ሕጉ ፍትሃዊ መሆኑን፣ አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ለሃገሪቱ አስፈላጊ መሆኑን ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም እንዲሰረዝ ሲንቀሳቀስ የነበረው። ቀደም ሲል እንደጠቀሰኩት የፀረሽብርተኝነት ሕጉን መቃወም በቀላሉ አጨብጫቢ ያስገኝልኛል ከሚል የተሳሳተ ሥሌት በመነሳት እንጂ።

እዚህ ላይ “አንድነት አጨብጫቢ ለምን ፈለገ?” የሚል ጥያቄ የሚያነሱ ሊኖሩ ይችላሉ። አንድነት ከጀርባ ያለውን አደጋ ከግምት ሳያስገባ፣ ጭብጨባ ሸመታ ላይ ብቻ አተኩሮ የአክራሪዎችና የአሸባሪ ጀሌዎች መለጠፊያ የሆነው በምርጫ ካልተሳካ በአመፅ መንግስትን የመጣል አካሄድን ተስፋ ስላደረገ ነው። አንድነት ይህን አቋሙን ህዳር 2005 ላይ ባካሄደው ስብሰባ ማሳወቁ ይታወሳል። በዚህ ስብሰባ ላይ የፓርቲው  የፓርቲው የፖለቲካ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሙላቱ ጣሰውና በወቅቱ የፓርቲው ሊቀመንበር የነበሩት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ባቀረቧቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ‘ኢህአዴግን በምርጫ ማሸነፍ ስለማይቻል ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መፈጠር አለብን’ የሚል አቋም ይዘው እንደነበረ ይታወሳል።

ይህ የአንድነት አካሄድ ሕዝባዊ መሰረት እንደሌለው በመረዳቱ በምርጫ በሚገኝ ውክልና ወደሥልጣን ለመውጣት እንደማይችል አስቀድሞ ከማወቅ የመነጨ ነው። አንድነት አጨብጫቢ መሸመት ያስችላል ብሎ የገመተውን አጀንዳ እንዲያነፈንፍ ያደረገው ይህ ተጨባጭ ሁኔታ ነው።

አንድነት ሰሞኑን በሰጠው መግለጫ ይህንኑ ርካሽ ጭብጨባ የመሸመት አካሄድን የሚያመለከት መልዕክቶች አስተላልፏል። ከእነዚህ መሃከል “መንግስት ለ2007 ምርጫ

ፍጆታ ሲል ለሰራተኛው ደሞዝ ጨመርኩ ቢልም፣ ሕዝቡ በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ነው።" የሚለው አንዱ ነው።

አንድነት፣ የሃገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ተከትሎ የተከሰተውና በተለይ ቋሚ ገቢ ያላቸውን ዜጎች - በአመዛኙ የመንግስት ሰራተኞች ላይ ጫና ያሳደረውን የኑሮ ውድነት ለተቃውሞ መቀስቀሻነት ለመጠቀም ተደጋጋሚ ሙከራ ማድረጉን እናስታውሳለን። ከወራት በፊት ያካሄደው "የእሪታ ቀን" የተሰኘ ቀፋፊ ሥያሜ የተሰጠው የተቃውሞ ጥሪ ላይም የኑሮ ውድነት አንዱ መቀሰቀሻ ነበር።

መንግስት የኑሮው ውድነት ከጀመረበት 1999 ዓ/ም ጀምሮ በተለይ የመንግስት ሰራተኛው የዋጋ ንረቱን መቋቋም እንዲችል የደሞዝ ማሻሻያ እርምጃዎችን ወስዷል። በ1999 ማብቂያ ላይ እንዲሁም በ2003 ላይ የተደረገውን የደሞዝ ማሻሻያ ለዚህ አሰረጂነት መጥቀስ ይቻላል። ከደሞዝ ማሻሻያው በተጓዳኝ በተለይ ተገቢ ባልሆነ የንግድ አሰራር ምክንያት የሚፈጠር የዋጋ ንረትን መከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን ወስዷል። በየቀበሌው የሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ መደረጉን፣ በአብዛኛው ከተሜ የመግዛት አቅም ላይ ጉልህ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የተወሰኑ ሸቀጦች ላይ የዋጋ ቁጥጥር እንዲሁም ድጎማ ማደረጉ፣ በመጨረሻም የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ እንዲወጣ መደረጉ ተጠቃሾች ናቸው።

እነዚህ በመንግስት የተወሰዱ እርምጃዎች የመንግስት ሰራተኞችና አጠቃላይ ህዝቡ የኢኮኖሚ እደገት ባስከተለው የዋጋ ንረት እንዳይጎዳ ተከላክለውለታል። ባለፉ ሁለት ተኩል አመታት የተወሰዱ የገንዘብ ግሽበትን መከላከያ የገንዘብና የታክስ ፖሊሲዎች የገንዘብ ግሽበት መጠኑን በአንድ አሃዝ ላይ ረግቶ እንዲቆይ ማድረግ አስችሏል። አሁን የግሽበት መጠኑን መቆጣጠር ቢቻልም የ2003 የደሞዝ ማሻሻያ ከተደረገ በኋላ የጨመረውን ዋጋ የመንግስት ሰራተኛው እንዲቋቋም በቅርቡ የተደረገው የደሞዝ ማስተካከያና የነፃ ትራንስፖርት አገልግሎት የሰራተኛውን ኑሮ ማሻሻልን ዓላማ ያደረገ ነው። እነዚህ እውነታዎች የሰሞኑ የደሞዘ ማስተካከያ ከመጪው ምርጫ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ከዚህ ቀደም ሲደረጉ ከነበሩት ጋር ተመሳሳይ የሆነ የሰራተኛውን ኑሮ፣

ኢኮኖሚው የግድ ከሚለው የገበያ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ኑሮውን የማሻሻል ዓላማ ብቻ ያለው መሆኑን ያመለክታሉ።

አንድነት ያልተረዳው ወይም መረዳት ያልፈለገው ነገር መንግስት በባለፈውም ሆነ በአሁኑ የመንግስት የስልጣን ዘመን፣ ምርጫ ባልተቃረበባቸው ወቅቶች የመንግስት የሰራተኞች ደሞዝ  ማሻሻያ እንዲሁም የተወሰኑ ሸቀጦች ላይ የስርጭትንና የመሸጫ ዋጋ ቁጥጥር ሲያደርግ ቆየታል።  ሕዝቡም ይህን ያውቃል። የተወሰኑ በሥርአቱ ላይ ጭፍን ጥላቻ ያላቸው ካልሆኑ በስተቀር በቅርቡ የተደረገው 'የደሞዝ ማሻሻያው የምርጫ ማባባያ ነው' የሚለውን የአንደነት ወሬ አምኖ የሚቀበል የለም።

አንደነት ከዚህ ቀደም ሕዝቡን በቀላሉ አነሳስቼ ደጋፊዬ አደርጋለሁ ብሎ ያሰበው የኑሮ ውድነት አጀንዳ መንግስት በወሰዳቸው እርምጃዎች እጁ ላይ ጋሸቦበታል። በመሆኑም ይህን የጋሸበ አጀንዳው ጠንከሮ እንዲቆምለት የደሞዝ ማሻሻያው ለቀጣዩ ምርጫ ድጋፍ ለማግኘት የተደረገ አስመስሎ ማቅረብን ወደደ። አንደነት የሰሞኑ መግለጫ ላይ ይህን አጀንዳ ያነሳው ለዚህ ነው።

አንድነት በሰሞኑ መግለጫው ሌላ ጉዳይም አንስቷል። ይህም "መንግስት የአዲስ አበባን ይዞታ ለማስፋፋት ሲል የሚመለከታቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ሳያወያይ  ባደረገው አከላለል በተነሳ የህዝብ ቁጣ ባለፈው ዓመት በርካታ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቸ ለሞት ተዳርገዋል፣ ይህ ያለፈውን ዓመት መራራ አድርጎታል።" የሚል ነው።

በቅድሚያ ባለፈው ዓመት በተወሰኑ የኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ተቀሰቀሶ በነበረው ሁከት አንድም የዩኒቨርሲቲ ተማሪ አልሞተም። አንድነት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሞተዋል በሎ የተናገረወ ፍፁም ውሸት ነው።

ከዚህ በተረፈ  አሁን ሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደሚያውቁት፣ በተለይ ሁሉም የኦሮሚያ ተወላጆች እነደሚያውቁት በፊንፊኔ ወይም በአዲሰ አበባና በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን መሃከል ምንም አይነት አዲስ የወሰን መካለል አለተከናወነም።

የሁለቱ ተጎራባች አሰተዳደሮች ማለትም የፊንፊኔ/አዲሰ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ነዋሪዎች ሊለያይ የማይችል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትስስር አላቸው። ይህ በአዋጅ የተፈጠረ ትስስር ሳይሆን የህዝብ ለህዝብ ነፃ ግንኙነት የፈጠረው ነው። ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳውም ትልቅ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በውሃና በአየር ብክለት አንዱ ሌላው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል የሚችልበት ሁኔታ አለ።

በመሆኑም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ግንኙነቱ የሁለቱንም አስተዳደር ነዋሪዎቸ የተሻለ ተጠቃሚ ማድረግ በሚያስችል ሀኔታ የተቀናጀ ለማደረግ፣ እንዲሁም አነዱ ሌላው ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅእኖ ለማሰወገድ የተቀናጀ የጋራ መሪ ዕቅድ ያስፈልጋቸዋል። በዚህ መሰረት የፊነፊኔ/አዲሰ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የጋራ የተቀናጀ መሪ ዕቅድ ተዘጋጀ፤ የተደረገው ይሄው ነው።

ይህ እቅድ የአንዱን መሬት አሳለፎ ለሌላው አይሰጥም፤ አነዱ በሌላው አሰተዳደራዊ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ አይፈቅድም። የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን እነደተቀሩት የኦሮሚያ ክልላዊ ዞኖች ሕዝቡ በመረጣቸው ተወካዮች ራሱን ችሎ ነው የሚተዳደረው፣ በኦሮሚኛ ቋንቋ ነው የሚሰራው፣ የልዩ ዞኑ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮሚኛ ቋንቋ ነው የሚያስተመሩት . . .።

እንግዲህ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች የጋራ መሪ ዕቅዱን መነሻ በማደረግ ሁከት ተቀስቅሶ የነበረው እውነት መሪ ፕላኑ የበኦሮሚያና በአዲስ አበባ መሃከል አዲስ የወሰን መካለል ስላደረገ አልነበረም። ዕቅዱን የወሰን መካለል አስመስለው ያቀረቡት አንደነትን ጨምሮ ከሁከትና ብጥብጥ እናተርፋለን በለው የሚያስቡ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ናቸው። አነአንድነት የመሪ ፕላኑን ዓላማ ሆን ብለው በተሳሳተ መንገድ ተርጉመው የነዙትን ወሬ፣ ኦሮሚያን ገንጥዬ ነፃ መንግስት እመሰርታለሁ ብሎ ጥቂት ገለሰቦችን የዞ ሸአቢያ ጉያ የተወሸቀው ኦነግና በይፋ የሻአቢያ ተላላኪነቱን ያወጀው ግንቦት 7 የተሰኙት አሸባሪ ቡድኖች ተቀበለው በማራገብ ውዥንብርሩን በተወሰነ ደረጃ አቀጣጥለውታል። የኦሮሚያን መሬት በመቸብቸብ ለመበልፀግ ያቀዱ ኪራይ ሰብሳቢዎችም ግልፅ የልማት እቅድ ከዚህ የዘረፋ እቅዳቸው ስለሚያናጥፋቸው ውዥንብር ፈጠራውን ተቀላቀለውት ነበር።

ይህ በአነአንድነት ሆነ ተብሎ የተነዛው ወሬ በተለይ በአምቦ ከተማ በቀሰቀሰው ሁከት የግለሰቦችና የመንግስት ንብረት ወድሟል። የሰውም ህይወት ጠፊቷል፤ ልብ በሉ አንድም የአምቦ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ግን አልሞተም። ለዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ተጠያቂው መንግስት ሳይሆን በሃሰተኛ ወሬ ሁከቱ እንዲቀሰቀስ ያደረጉት ወገኖች ናቸው፤ አንድነት ይህን ተጠያቂነት ቢያንስ በሞራል ተጠያቂነት ደረጃ ይጋራዋል የሚል እምነት አለኝ።

አንድነት የዚህ አይነት ግልፅ የሆነ ሃሰተኛ ወሬ መንዛትና ማራገብ የፈለገው፣ አንድ ከሁከቱ ትርፍ ይገኛል በሎ ሰለሚያስብ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት ነው። በዚህ ሃሰተኛ ወሬ የተፈጠረው ውዥንብር እየጠራ ሲሄድ አንደነት በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ እውነተኛ ማንነቱ ቁልጭ ብሎ የታየ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኦሮሞ ህዝበ አንደነት ፓርቲን መቼም እንደአጋሩ ተመልክቶት እነደማያውቅ መታወቅ አለበት። ለወደፊትም እንደአጋሩ እነዲመለከተው የሚያደርግ አንዳችም ነገር የለም።

የኦሮሞ ህዝብ አንድነት ፓርቲን እንደአጋሩ የማይመለከተው፣ ለዘመናት ተጭኖት የነበረውን ብሄራዊ ጭቆና ከፍተኛ የህይወት መስዋዕተነት በጠየቀ መራራ ትግል አሽቀንጥሮ ጥሎ የተጎናጠፈውን በሄራዊ ነፃነት፤ ራሱን በራሱ የማስተዳደር፣ በቋንቋው የመንግስት አገልግሎት የማግኘት፣ የመማር፣ ባህሉን የማሳደግ፣ ታሪኩን የመንከባከብ . . . መብትና ነፃነት የማይቀበል በመሆኑ ነው።

አንድነት ፓርቲ የኦሮሞ ሕዝብ ራሱን በራሱ እያስተዳደረ ከሌሎቸ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በእኩለነትና በመከባበር ላይ በተመሰረተ አንደነት የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ሥልጣን ባለቤት ሆኖ መኖር ያስቻለውን ፌደራላዊ ሥርአት አይቀበልም። የኦሮሞ ሕዝብ ይህን ያውቃል።

አንድነት የፌደራላዊ ሥርአቱ አወቃቀር በብሄራዊ ማንነት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በተራራ፣ በገደል . . . እነዲሸነሸን ይፈልጋል። ይህ ሁኔታ የኦሮሞን ሕዝብ አምስት ስድስት ቦታ በመከፋፈል፣ ከአምስት ስድስት ሌሎች ብሄሮች ጋር በመጨፍለቅ ብሄራዊ ጥንካሬው እንዲዳከም፣ የማንነቱ መለያዎቹ የሆኑት ቋንቋውና ባህሉ እንዲደበዝዝ

ያደርጋል። በዚህ ሁኔታ ራሱን በራሱ ማስተዳደር አይችልም። የኦሮሞ ህዝብ አንድነት ፓርቲ ይህን እንደደገሰለት ያውቃል።

አንደነት ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ ላይ የጠቀሰውን 'በፊንፊኔና በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን መሃከል የወሰን መካለል ተደረገ' በሚል ሃሰተኛ ወሬ ያወራው የኦሮሞን ሕዝብ አደናግሮ ሕገመንግስታዊ ሥርአቱን በኃይል ለመናድ ሥውር ተልዕኮ ሊማግደው መሆኑንም የኦሮሞ ሕዝብ ያውቃል። የኦሮሞ ሕዝብ ይህን እንደንቀትም ነው የሚቆጥረው። ይህ ደግሞ ቀደሞም በውስጡ የነበረውን  አንድነት ፓርቲን ያለመፈለግ ወደተቃውሞነት እንዲያድግ ማድረጉ አይቀሬ ነው። ይህ ኦሮሞዎች በአንድነት ላይ ያላቸው እውነተኛ ሥሜት ነው።

እንግዲህ አንድነት በሰሞኑ መግለጫው ያስተላለፈው መልዕክት በመጪው ምርጫ ላይ በመሳተፍ በህዝብ ውክልና ስልጣን ለመጋራት፣ ከሆነም ለመረከብ ከመሥራት ይልቅ በህዝብ ውስጥ ውዥንብር በመንዛት ሥልጣን ለመመንተፍ ያስችላል ያለውን 'ሕዝባዊ ንቀናቄ' የተሰኘ የአመፅ እንቅስቃሴ ለማስነሳት ያሰበ መሆኑን ያመለክታል።

በመግለጫው በ1997 ምርጫ እነደታየው ሕዝብ በመንግስት ላይ መሰረተ ቢስ ጥላቻ እንዲያድርበት በማደረግ የተሻለ አማራጮች ሳይኖሩት በጥላቻ የተገፋ የህዝብ ድምፅ የማግኘት ፍላጎት ያለው መሆኑንም አሳይቷል። ከምርጫ 97 ወዲህ አንድ አስርት ዓመት ተቆጥሯል። የህዝቡም አመለካከት የዛኑ ያህል ተቀይሯል። ሕዝብ  አንዱ ወገን ላይ ጥላቻ ስላደረበት ብቻ የተሻለ አማራጭ የሌለውን ሌላ ወገን ወደመምረጥ ይሄድ የነበረበት ሁኔታ አሁን ተቀይሯል። የጥላቻ ፖለቲካ ግዜው አለፏል። አንድነት ግን አሁንም አስር አመታት ወደኋላ ቀርቶ፣ ከመሰረተ ቢሰ ጥላቻ (prejudice) ፖለቲካ ለማትረፍ ይመኛል።

በአጠቃላይ አንደነት ሰሞኑነ ካወጣው መግለጫ፣ ፓርቲው የህዝቡን መብቶችና ነፃነቶች፤ ፍላጎትና ጥቅሞች ያገናዘበ ፖሊሲ ቀረፆ በሕዝብ ውክልና ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚያስችል ሰላማዊ የምርጫ እንቅስቃሴ ከማድረግ ይልቅ፣ 'ሕዝባዊ ንቅናቄ' በተሰኘ የከተማ ሁከት፣ ይህ ካልተሳካም በመሰረተ ቢስ ጥላቻ የሚነዳ ድምፅ በመሸመት ወደሥልጣን መምጣትን ተስፋ ማድረጉን እንረዳለን።

ይህ የህዝብን በቸኛ የሥልጣን ምንጭነትና ባለቤትነትን የሚፃረር የአንድነት አካሄድ ተገቢ ሥላልሆነ  ራሱን ማስተካከል ይጠበቅበታል። አንድነት የሚያዛልቀው መንገድ የህዝብ የሥልጣን ውክልና የሚረጋገጥበት ምርጫ ብቻ መሆኑን ተገንዝቦ በውስጡ ያለውን ድርጅታዊ ችግር ቅድሚያ ሰጥቶ በመፍታት ወደሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መምጣት አለበት። ህዝብ ምርጫ በመጣ ቁጥር የግልና የቡድን ፍላጎታቸውን ላዩ ላይ ለመጫን በሚራወጡ ወገኖች የሁከት አካሄድ መዋከብ አይፈልግም። ‘ምርጫ መጣ ረብሻ ውጣ’ የሚልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።